ይህ መጽሃፍ በስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች በሚነገሩ በሚከተሉት ቋንቋ ዎች ተዘጋጅተዋል።

- አማረኛ
- ካምቦዲያን
- ቻይና
- ላኦ
- ሶማሊኛ
- ስፓኒሽ
- ትግሪኛ
- ቬትናሚኛ

© Community Training and Assistance Center, 2005
Boston, MA

የቤተስብ ድጋፍ ፕሮግራም
ስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች
ስያትል ፤ ዋሽንግተን

የገንዘብ ድጋፍ የተገኘው
ከአሜሪካ የትምህርት ክፍል
ትምህርት ለማሻሻል ከተመደበው ባጀት ነው

*AMHARIC*

# ተማሪዎች ጥሩ የትምህርት ውጤት እንዲኖራቸው ተባብረን እንስራ

ለ የስያትል ህዝባዊ ት/ቤቶች ወላጆችና ኮሚዩኒቲዎች የተዘጋጀ ጠቃሚ መጽሓፍ

## ማስታወሻ

## ተጨማሪ ጠቃሚ ምንጮች

- ወደ ትምህርትቤትዎ ወይም ከስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች አስተዳደር ጽህፈት ቤት ጋር ለመገናኘት በምትፈልጉበት ጊዜ

  Seattle Public Schools
  John Stanford Center for Educational Excellence
  2445 3rd Avenue South
  PO Box 34165, Seattle, WA 98134
  (206) 252-0000
  www.seattleschools.org

- ስያትል ህዝባዊ ቤተመጽሓፍቶች ( በስያትል የሚገኙት ሁሉ)
- ማንም ህጻን ወደኋላ አይቀርም (www.nclb.gov)
- ብሄራዊ የወላጆች አስተማሪዎች ማህበር (www.pta.org)
- ኮሚዩኒቲ ስልጠና እና ድጋፍ ማእከል (www.ctacusa.com)

<u>ሌሎች ሀሳቦች ወይም አስተያየቶች:</u>

- ____________________________________________
- ____________________________________________



## መግቢያ

### ሁሉም ተማሪዎች ጥሩ የትምህርት ውጤት ማምጣት ይችላሉ

ይህ መጽሓፍ በተለይ ተማሪዎች በትምህርታቸው ጥሩ የትምህርት ውጤት እንዲያመጡ ለማድረግና ለመተባበር ፍላጎት ላላቸው ለወላጆች፤ የኮሚዩኒቲ አባሎች እና የትምህርትቤቱ ሰራተኞች ተብሎ የተዘጋጀ ልዩ መጽሃፍ ነው።

ወላጆች,[1] ትምህርትቤቶችና የኮሚዩኒቲው አባሎች[2] ተማሪዎችን ለመርዳት በተለያዩ መንገድ ትብብራቸውን ያሳያሉ። ሁሉም በጣም ጠቃሚ የሆነ አስተዋጽኦ አላቸው። ጥሩ የትምህርት አሰራርና ሲስተም እንዲኖር አንድ ላይ በመተባበር ይሰራሉ።

ወላጆች፤ ትምህርትቤቶችና የኮሚዩኒቲው አባሎች አንድ ላይ ተባብረው በመስራት የሚከተሉትን ውጤት ማምጣት ይችላሉ።

- ከሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸው ነገር
- በየትምህርትቤቶች፤ በቤት እና እንዲሁም በኮሚዩኒቲው ጥሩ ድጋፍ የሚገኝበት የትምህርት ስርኣት።
- ጥሩና ከፍተኛ ጥራት ያለው የትምህርት ፕሮግራሞች እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ የትምህርት ቁሳቁሶች፤ ጥሩ ችሎታ ያላቸው አስተማሪዎች እና እንዲሁም ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ተጨማሪ ድጋፍ እንዲያገኑ ማድረግ።
- ልዩ የትምህርት ቡድን እንዲኖር ማድረግ ከ (ተማሪዎች፤ትምህርትቤቶች ቤተሰቦች እና ኮሚዩኒቲ የተውጣጡ)

በወላጆችና በትምህርትቤቱ መሃከል ጥሩ ዝምድና እንዲኖር እንዲሁም እያንዳንዱ ህጻን በሁሉም ትምህርትቤቶች ጥሩ የአካዳሚክ ትምህርት እንዲኖራቸው ለማደረግ በተለይ መረጃዎች መለዋወጥ፤ ጥያቄዎች መጠየቅና ለጥያቄዎቹ በጋራ መፍትሄ መፈለግ የመሳሰሉ አሰራር በጣም ትልቅ አስተዋጽኦ አለው።

---

[1] “ወላጅ” ማለት የልጆች አሳዳጊ ወይም ሞግዚት ወይም አያቶች

[2] “የኮሚዩኒቲው ማህበር” ማለት መንግስታዊ፤ አትራፊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሃይማኖት እምነት የሚከተሉ ማህበሮ።ለምሳሌ የቤተሰብ ማእከል፤ ሶሻል አገልግሎት ማእከል፤ የወጣቶች ማህበር፤ የወላጆች ማህበር፤ ቤተክርስቲያን እንዲሁም ሌሎች ማህበሮች።

## አስፈላጊና ጠቃሚ ምንጮች

### ስያትል ህዝብዊ ት/ቤቶች የቤተስብ ሽርክና መመሪያ

*“የዚህ ፖሊሲ ወይም መመሪያ የስያትል ትምህርትቤቶች ቦርድ አላም ሲሆን ዋና አላማው ወላጆች በትምህርትቤቶች፣ በቤት እንዲሁም በኮሚዩኒቲው እንዲሳተፉ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግና ለማበረታታት ነው። ወላጆች ከተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍል የመጡ እና የተለያየ ባህልና ልምድ ያላቸውም በመሆናቸው ይህም በተለይ ለተማሪዎቹ ትምህርት መማር በጣም ትልቅ ጠቃሚ አስተዋጽኦ እንዳለው የትምህርትቤቱ ቦርድ ትልቁ እምነት ነው ስለሆነም በስያትል ትምህርትቤቶች ማለት በሁሉም ትምህርትቤቶች በወላጆችና በትምህርትቤቶች መሃከል ጥሩና ጠንካራ የሆነ ዝምድና እንዲኖር የትምህርትቤቶች ቦርድ የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል”*
(የስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች ፖሊሲ F05.00, ኦጎስት 2004)

### ለወላጆችና ኮሚዩኒቲ ተጨማሪ የትምህርትቤቶች ቦርድ መመሪያ ወይም ፖሊሲ:

- ከኮሚዩኒቲ ጋር ግንኙነት
- ወላጅና አስተማሪ ማህበር
- የዜጎች አማካሪ ቡድን እና ኮሚቴ
- ህዝባዊ ተሳትፎ በየቦርዱ ስብሰባዎች
- የዜጎች አማካሪ ኮሚቴ አሰራር
- ነጻ አገልግሎት የሚሰጡ
- የዜጎች ህግን ማክበር አሰራር
- ትምህርትቤት ለሚጎበኙ
- የኮሚዩኒቲው ትብብር

እነዚሁ እና ሌሎች ከተማሪዎች፣ ከትምህርትቤቱና ትምህርት አይነቶች ጋር የተያያዙ ተጨማሪ መመሪያዎች በ የስያትል ህዝብዊ ትምህርትቤቶች ዌብ ሳይት ማግኘት ይቻላል (www.seattleschools.org) ወይም ዋና አስተዳደር ክፍልን ማነጋገር ትችላላችሁ።

## 8. ጥያቄዊችና አሳሳቢ ነገሮች

### ግንኙነት

ጥሩ የትምህርት አሰራር እንዲኖር ከተፈለገ በወላጆች፣ ኮሚዩኒቲውና በትምህርትቤቱ መሃከል ጥሩና ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖር ይፈለጋል። ሁሉም አንድላይ በመስራትና፣ የተለያዩ መረጃዎች አንድላይ በመለዋወጥና የተለያዩ ጥያቄዎች በማቅረብና በጋራ መፍትሄ በመፈለግ መስራት ለተማሪዎች ትልቅ አስተዋጽኦ አለው።

**ጥቆማ**

- **ወላጆችና አስተማሪዎች ትምህርት በሚጀመርበት የመጀሪያ አመት፣ ቀጠሮ በመያዝ በቤት ወይም በትምህርትቤት፣ በኮሚዩኒቲ በሚደረጉ ስብሰባዎች እና በኮንፍረስን በአካል በመገናኘት ከአስተማሪው ጋር መገናኘት**
- **ትምህርትቤቶች ወላጆች ከ የትምህርትቤቱ ዳይረክተር ጋር ተገናኝተው እንዲነጋገሩ ሁኔታዎች ያመቻቻሉ።**
- **ወላጆች፣የትምህርትቤት ሰራተኞች ወይም የኮሚዩኒቲው ሰራተኞች አስቀድመው ቀጠሮ በመያዝ ስለ ተማሪዎች የትምህርት እድገት ያላቸውን ጥያቄዎች መጠየቅና መወያየት ይችላሉ።**
- **ወላጆች፣ የትምህርትቤት ሰራተኞች እና የኮሚዩኒቲው ሰራተኞች በማናቸውም ሰአትና ጊዜ ተገናኝተው እርስበራሳቸው መነጋገር ይችላሉ።**
- **ትምህርትቤቶች በየስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች ፖሊሲ መሰረት ግላዊ የሆነ ማናቸውም መረጃ በምስጢር እንዲያዝ ያደርጋሉ።**
- **ወላጆች፣አስተማሪዎች እና ሌሎች የትምህርትቤት ሰራተኞች ስለ አንዳንድ ተማሪዎች የሚነሳ አንዳንድ ጉዳዮች ላይ ጉዳዩ ዳይረክተሩ ከማወቃቸው በፊት መፍትሄ ለማግኘት ይሞክራሉ።**
- **ወላጆች ወይም የኮሚዩኒቲው ተወካዮች መፍትሄ ላልተገኘለት ጉዳይ መፍትሄ ለማግኘት ከስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች የደንበኞ ክፍል ጋር ይነጋገራሉ። የጽህፈት ቤቱ ስልክ ቁጥር** (206) 252-0010.

**<u>ሌሎች ሃሳቦች:</u>**

- ________________________________________
- ________________________________________



## ይዞታዎች

ይህ መጽሃፍ ተማሪዎች ጥሩ የአካዳሚክ ትምህርት እንዲኖራቸው ለማደርግ የሚረዱ ስምንት አርእስቶች አሉት። እያንዳንዱ አርእስት በጣም ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችና ጥቆማ ይሰጣሉ።እነዚህ አርእስቶች መሰረት በማድረግም በወላጆች፣ በትምህርትቤቶችና በኮሚዩኒቲው መሃከል ጥሩ ግንኙነት እንዲኖር ለማድረግ ይቻላል። እንዲሁም በዚህ መጽሃፍ ላይ ሌላ ተጨማሪ ጠቃሚ መረጃዎችና ስልክ ቁጥሮች ማግኘት ይቻላል።


| <u>አርእስት</u> | <u>ገጽ</u> |
|---|---|
| 1.ወደ ትምህርትቤቱ እንኳን በደህና መጣችሁ፣ ጥሩ የትምህርት ቦታ | 3 |
| 2. የክፍል ውስጥ ትምህርት | 5 |
| 3. ሪፖርት ካርድ እና ፕሮግረስ ሪፖርት | 6 |
| 4. ደረጃውን የጠበቀ ፈተናዎች | 7 |
| 5. የትምህርት ፕላን ለየብቻ ለእያንዳንዱ ተማሪ | 9 |
| 6. ፕሮግራሞችና ትብብር ለተማሪዎች | 11 |
| 7. የትምህርትቤቶች አስተዳደር መሻሻሎች | 13 |
| 8. ጥያቄዎችና አሳሳቢ ነገሮች | 15 |

| <u>አስፈላጊና ጠቃሚ ነገሮች</u> | <u>ገጽ</u> |
|---|---|
| ማንም ህጻን ወደኋላ አይቀርም (NCLB) መግለጫ | 1 |
| የስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤት ቤተስብ ሽርክና ፖሊሲ | 16 |
| አስፈላጊ ጠቃሚ ምንጮች | 17 |


እባክዎትን በዚህ መጽሃፍ ስላሉ መረጃዎች ሃሳብ ተለወወጡ እንዲሁም የራስዎ የሆነ ሌላ አስተያየትና ሃሳብ ካልዎት ከሌሎች ጋር ሃሳብዎን ያካፍሉ።

## ማንም ህጻን ወደኋላ አይቀርም (NCLB)

NCLB ይህ ብሄራዊ የትምህርት ህግ ነው።የዚህ ፕሮግራም ዋና አላማ NCLB ሁሉም ህጻናቶች ያለ ምንም አድልዎ እኩል የትምህርት እድል እንዲያገኙና እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው። በዚህ ፕሮግራም NCLB, ሁሉም ህዝባዊ ትምህርትቤቶች የሁሉም ተማሪዎች የትምህርት ውጤት ማሳየት መቻል አለባቸው።ትምህርትቤቶች ሁሉ ብቃታ ያላቸው አስተማሪዎች እንዲኖራቸው ይደረጋል።

NCLB ፕሮግራም መሰረት ወላጆች የልጆቻቸው የትምህርት ውጤት እና እድገት የማወቅ መብት አላቸው።እንዲሁም በየልጆቻቸው ትምህርት ላይ ፕላን የማውጣትና መፍትሄ የመፈለግ እንዲሁም ትምህርትቤቶችና የትምህርትቤቶች አስተዳደር ለማሻሻልና ለውጥ ለማምጣት በሁሉም ነገር የመሳተፍና ሃሳብ የመስጠት ሙሉ መብት አላቸው።

የ NCLB ህግ በየአሜሪካ ኮንገርስ ውሳኔ ህጉ የጸደቀው በ2002 አመተ ምህረት ላይ ነው። የሚከተሉት ዝርዝሮች ስለ ህጉ የሚያስረዱ ነጥቦች ናቸው።



### ጥቆማ

- ትምህርትቤት እና ወላጆች የወላጆችና አስተማሪ ማህበር በእያንዳንዱ ትምህርትቤት እንዲቋቋም ማድረግ። ለተማሪዎች እና ለትምህርትቤቱ እድገት ሊረዳ የሚችል አጀንዳዎች ማዘጋጀት
- ትምህርትቤቶች፤ ወላጆች እና የኮሚዩኒቲው አባሎች በሚካሄዱት ስብሰባዎች በመገኘት ስለ ትምህርትቤቱ እድገት ማየት እና መወያየት የተገኙትን ጥሩ ውጤቶች ማበረታታት እንዲሁም ችግሮች ካሉም መፍትሄ እንዲያገኙ ማድረግ።
- የትምህርትቤት ሰራተኞችና ወላጆች ለእያንዳንዱ ትምህርትቤት ለወጥ የሚያመጣ ፕላን ማዘጋጀት። በየአመቱ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባ ለውጦች ቅድሚያ በመስጠት ደረጃ በደረጃ ትምህርትቤቱ እንዲሻሻል ማድረግ።
- የትምህርትቤት ሰራተኞችና ወላጆች የትምህርትቤቱ ባጀት ስለ ገንዘብ ወጪና ገቢ ለማጽደቅና ውሳኔ ለማሳለፍ በሚደረገው ስብሰባ ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ይደረጋል።
- ወላጆች በስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች ስለ ትራንስፖርት፤ ስለ አዲስ ፕሮግራሞችና የተለያዩ ፖሊሲዎች ምክር ለመስጠት በሁሉም ኮሚቴ ወይም አማካሪ ኮንስል ወስጥ በንቃት ተሳታፊ እንዲሆኑ ይፈለጋል።
- ወላጆች መቼ የትምህርትቤቶች ቦርድ ስብሰባ እንደሚያካሄዱ ቀኑ እንዲያውቁት ይደረጋል።በዚሁ ጊዜ ወላጆች ተገኝተው ያላቸው አስተያየትና መስጠት እንዲሁም መፍትሄ በመፈለጉ ላይም ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይፈለጋል።ድምጻቸው ማሰማት አለባቸው።
- የኮሚዩኒቲው ማህበሮች ለትምህርት የሚያስፈልጉ ነገሮች ለይቶ ማወ እና ያሉትን እድሎች ዘርዝሮ ማወቅ።ችግሮችን ለይቶ ማወቅ እንዲሁም ለችግሩ መፍትሄ ለማግኘት ከወላጆች እና ከትምህርትቤቱ ጋር በጋራ ተባብሮ መሰራት።

**<u>ሌሎች ሃሳቦች:</u>**

- ________________________________________
- ________________________________________

## 7. የትምህርትቤት አስተዳደር መሻሻል

### ትምህርትቤቶችን ለማሻሻል

ለሁሉም ህጻናት የሚሰጥ ትምህርት ለማሻሻል የትምህርት ስርአቱ በየጊዜው መሻሻል አለበት።ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ የኮሚዩኒቲው መሪዎች እና የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ለሚያጋጥሙት አንዳንድ ችግሮች መፍትሄ ለማመጣት ሃሳብ በመስጠትና ንቁ ተሳይፎ በማድረግ ትምህርትቤትን ለማሻሻል አንድ ላይ በጋራ ተባበረው መሰራት አለባቸው።

ማንም ህጻን ወደኋላ አይቀርም (NCLB) በሚለው ህግ መስረት ትምህርትቤት ለማሻሻል ፕላን በሚወጣበት ጊዜ ወላጆችም ፕላን በማውጣቱ ስራዎች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ይፈለጋል።የትምህርትቤት አስተዳደርም ስለ ተሰሩ ስራዎች በየጊዜው ለወላጆችና ለኮሚዩኒቲው ማስታወቅ አለባቸው። በሪፖርቱ ውስጥም ስለ የትምህርትቤቱ የዋስል ፈተና ውጤቶችና ሌሎች መረጃዎች ማለት ስለ የተማሪዎች ብዛት ምን ያህል ተማሪዎች ሁለተኛ ደረጃ እንደሚጨርሱ የመሳሰሉት መረጃዎች በሪፖርቱ ውስጥ መካተት አለባቸው።

ወላጆች፣ ትምህርትቤቶች እና ኮሚዩኒቲው ማህበሮች ዝርዝር ሪፖርቱንና ትምህርትቤት ለማሻሻል የተነደፈውን ፕላን በጋራ ከተመለከቱት በኋላ ትምህርትቤቱ እንዲሻሻል ጥረት ያደርጋሉ።



| | |
|---|---|
| የተማሪዎች ችሎታና ውጤት | • በህዝባዊ ትምህርትቤቶች የሚማሩ ተማሪውች ሁሉ ችሎታቸው ለመለካት ደረጃው የጠበቀ ፈተና እንዲፈተኑ ይደረጋል።<br>• የተገኘው ውጤትም በየአመቱ የተገኘው መሻሻል ይለካል።<br>• በዋሽንግተን ስቴት የሚገኙ ትምህርትቤቶች የዋስል ፈተና ይሰጣሉ። ትምህርትቤቶች ለአካለስንኩል ለሆኑ አንዳንድ ተማሪዎች የተለየ መለኪያ ፈተና ማዘጋጀት ይችላሉ።<br>• ትምህርትቤቶች ተማሪዎች ያገኙትን የፈተና ውጤት ወላጆች እንዲያውቁት ይላክላቸዋል። |
| የአስተማሪዎች ችሎታ | • በ2005 2006 አመት መጨረሻ ላይ ሁሉም አስተማሪዎች በሁሉም የትምህርት አይነት ከፍተኛ ችሎታ እንዲኖራቸው ይፈለጋል።<br>• ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው አስተማሪዎች ሙሉ ሰርቲፊኬት፣ የባችለር ዲግሪ እና የትምህርት አይነት በማስተማር ጥሩ ችሎታ ያላቸው መሆን አለባቸው። |
| የትምህርትቤት እድገት | • በየአመቱ የትምህርትቤቶች አስተዳደር ስለ እያንዳንዱ ትምህርትቤት እድገት መሻሻል እና ስለ አስተማሪዎች ችሎታ ዝርዝር መረጃ ለወላጆች እና ለኮሚዩኒቲው ያቀርባሉ።<br>• ለአንድ አመት ወይም ሁለት አመት በተከታታይ ትምህርትቤቶች ድክመት ካሳዩ:<br>– የትምህርትቤቶች አስተዳደር ይህንን ለወላጆች ማሳወቅ አለባቸው በተጨማሪም ይህን ለማሻሻል ወላጆች እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ ይገልጻሉ።<br>– ትምህርትቤቶች ምንም አይነት ማሻሻል ካላሳዩ በሰወስተኛው አመት ተማሪው ልዩ ተጨማሪ የትምህርት ድጋፍ የማግኘት መብት አላቸው።(ተጨማሪ የትምህርት አገልግሎት).<br>– ወላጆች ልጆቻቸው ወደ ሌላ ጥሩ ትምህርትቤት የማዛውር እድልም ይሰጣቸዋል። |
| የት/ቤት ደህንነት | • ስለ ትምህርትቤቶች ደህንነት እና ሌሎች መረጃዎች ሁሉ ወላጆች ትምህርትቤቶች እና የኮሚዩኒቲ መሪዎች እንዲያውቁት ይደረጋል።<br>• በትምህርትቤት ውስጥ በሚፈጠረው አደጋ ጉዳት የደረሰባቸው ተማሪዎች ወላጆች ሌላ ትምህርትቤት የመቀየር እድል ይሰጣቸዋል። |
| ትምህርትቤት መሻሻል | • የትምህርትቤቱ አስተዳደር ትምህርትቤቶች ለማሻሻል ጥሩ የትምህርት ስርአት እንዲኖር ለማድረግ በሚያካሂዱት ጥረት እና ፕላን በማውጣት ስራዎች ላይ ወላጆች በንቃት እንዲሳተፉ ያበረታታል። |

## 1. ትምህርትቤቶች ሰላማዊ ቦታና ጥሩ የትምህርት መማር ስፍራ ናቸው

**ትምህርትቤት ጉብኝት**

የስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች ወላጆችን እና የኮሚዩኒቲው አባሎችን በክፍል ውስጥ በመገኘት እንዲሁም በአንዳንድ የትምህርትቤቱ ስራዎች ላይ ንቁ የሆነ ተሳታፊነት እንዲኖራቸው አስተዳደሩ ያበረታታል። ወላጆች በማና ቸው ጊዜና ሰአት ክፍል ውስጥ መጥተው ተማሪዎች ሲማሩ ማየት እና እንዲሁም መታዘብ ይችላሉ። ወላጆች ወይም ሌሎች ስዎች ለጉብኝት ወደ ትምህርትቤቱ በሚመጡበት በዋናው ጽህፈት ቤት በር በኩል መግባት ነው መግባት ያለባቸው።

**ደህንነትና የዲስፕሊን ፖሊሲ**

እያንዳንዱ ትምህርትቤት ጥሩ የትምህርት መንፈስ ያለው ጥሩ የደህንነትና የ ዲስፕሊን ፖሊሲ አላቸው። የፖሊስውን ኮፒ ከትምህርትቤቱ ጽህፈትቤት ማግኘት ትችላላችሁ።ወላጆች፤የትምህርትቤቱ ሰራተኞች እና የኮሚዩኒቲው መሪ ዎች ስለ ፖሊሲው ጥያቄ መጠየቅና ፖሊሲው ለማሻሻል አስተያየት መስጠ ት ትችላላችሁ።

ማንም ህጻን ወደኋላ አይቀርም በሚለው ህግ መሰረት በወላጆችና በኮሚዩኒ ቲው አባሎች መሃከል ስለ የትምህርትቤት ደህንነትና ስለ ተማሪዎች የእጽ ልምድ ችግር ያሉትን መረጃዎችን እንዲለዋወጡ ይፈለጋል።



**ጥቆማ**

- **ወላጆች፤** የትምህርትቤቶች ሰራተኞች እና የኮሚዩኒቲው አባሎች ሁሉ ልዩ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች እርዳታ እንዲ ያገኙ ለማድረግ አንድ ላይ በጋር በመተባበር ይሰራሉ።
- **ወላጆች** ከትምህርት ቤት ውጭ ተማሪዎች ሌላ ትምህርታዊ የ ሆነ ፕሮግራሞች ውስጥ የሚሳተፉ ከሆነ ይህንን ለአስተማሪዎ ች ያስታውቃሉ።
- **ወላጆች፤**የትምህርትቤቶች ሰራተኞችና ሌሎች አገልግሎት ሰጪ **ክፍል** በየጊዜም በመገናኘት ስለ ተማሪው የትምህርት ውጤት እና እንዲሁም አስፈላጊ ለውጦች እንዲደረጉ የሚፈለግ ከሆነ ም ይነጋገራሉ።

<u>ሌሎች ሃሳቦች:</u>

- ________________________________________
- ________________________________________

# 6. ፕሮግራሞችና ድጋፍ ለተማሪዎች

## ትምህርታዊ ድጋፍ

ከትምህርት በኋላ፣ ቅዳሜና እሁድ እንዲሁም በ በጋ ፕሮግራም ተማሪዎች የትምህርት ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል።የትምህርት ድጋፍ በትምህርትቤቱ ወይም በኮሚዩኒቲው ማእከሎች እና በ የሰፈሩ ቤተክርስቲያን በኩል ሊሰጥ ይቻላል።

ወላጆች ለልጆቻቸው የሚስማማና የሚመቸውን ፕሮግራም ለማግኘት ትምህርትቤቱን ወይም በአካባቢያቸው ከሚገኘው የኮሚዩኒቲው ማህበሮች በማነጋገር ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ።

በምንም ህጻን ወደኋል አይቀርም በሚለው ህግ መሰረት (NCLB) ትምህርትቤቶች ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ህጻናት ለይቶ በማወቅ ሁሉም ህጻናት ለሰዎስት አመት ለሚሆን ጊዜ ወይም ከዛ በላይ ነጻ የትምህርት ድጋፍ እንዲያገኙ ወይም እንዲሰጣቸው ህጉ ያስገድዳል። ይህ ድጋፍ የሚሰጥ ከሆነ ለማወቅ ልጅዎ የሚማሩበት ትምህርትቤትን ይጠይቁ።

የተማሪዎች አማላጅ ቡድን (SIT) ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሆነ በሌላ ለሚጋጥማቸው ችግሮ መፍትሄ ለማግኘት ይጥራሉ።ይህ ቡድን ከወላጆች፣ አስተማሪዎች፣ ኮንስላሮችና ሌሎች የትምህርትቤቱ ሰራተኞች የተውጣጡ አባሎች ይኖሩታል።

የግል የትምህርት ፕላን (IEP) ልዩ ድጋፍ እና እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች አካለ ስንኩል የሆኑ ልዩ የሆነ ፕሮግራም እና አገልግለቶች እንዲያገኙ ይደረጋል።ይህ ቡድን የተውጣጣው ከወላጆችና ትምህርትቤት ወይም አስፈላጊ ከሆነም ከኮሚዩኒቲው ሊሆን ይቻላል።



### ጥቆማ

- ወላጆች፣ የትምህርትቤት ሰራተኞች፣ ተማሪዎች እና የኮሚዩኒቲው አባሎች ከተለያዩ ህብረተስብ ክፍል የመጡ ስለሆኑ ያላቸውን ልምድ እና ልዩ ችሎታ ከሌሎች ጋር ልምዶችን መለዋወጥ።
- ትምህርትቤቶች:
  - ሁሉም ቤተሰቦች ተገናኝተው የሚወያዩበት አንዳንድ ፕሮግራሞች ማዘጋጀት።
  - የአስተርጓሚ አገልግሎትና ህጻን ልጅ የሚጠብቅ ሰው ማዘጋጀት
  - ወላጆችና የኮሚዩኒቲው አባሎች እንዲሁም የትምህርትቤቶች ሰራተኞች ነጻ ሆነው የሚወያዩበትና የሚሰበሰቡበት የመሰብሰቢያ አዳራሽ ማዘጋጀት።
  - አስፈላጊ ሲሆንም አንዳንድ ጊዜ ከትምህርትቤቱ ውጭ ለወላጆች አቅራቢያ በሆነ ስፍራ ማለት በኮሚዩኒቲው መሰበስቢያ አዳራሽ ስብሰባ ማካሄድ።
  - የተለያዩ ባህልና ህብረተሰብ እንዳሉ መገንዘብና እና ይህንን በተለይ በትምህርት ስርኣቱ ላይ እንዲጸባረቅ ማድረግ።
- ወላጆችና ትምህርትቤቱ በአደጋ ጊዜ እንዴት መገናኘት እንደሚችሉ ማወቅ።
- ወላጆች የትምህርትቤት አውቶቡስ የት እንደሚቆም ያውቃሉ።
- ወላጆችና የትምህርትቤቱ ሰራተኞች ስለ ደሕንነትና ዲስፒሊን ይወያያሉ በጋራም መፍትሄ ይፈልጋሉ።

ሌሎች ሃሳቦች:

- ______________________________
- ______________________________

## 2. የክፍል ውስጥ ትምህርት

### የተማሪዎች መማር

ወላጆች፤ የትምህርትቤት ሰራተኞች እና የኮሚዩኒቲው ማህበሮች ተማሪዎችን በበለጠ መንገድ መርዳት እና መተባበር ይችላሉ።

የስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች ተማሪዎች ሁሉ በሁሉም ክፍል ምንና ምን የትምህርት አይነት ማወቅና መማር እንዳለባቸው በሁሉም ትምህርትቤቶች የሚሰራ መመዘኛ ወይም ትምህርታዊ መለኪያ አላቸው። የትምህርትቤቶች መለኪያዎች ወይም መመዘኛ ኮፒ ለማግኘት ወይም ጥያቄ ለመጠየቅ ከፈለጋችሁ አስተማሪዎችን ወይም የትምህርትቤቱ ዳይሬክተር መጠየቅ ወይም ከ የስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች የኢንተርኔት ዌብሳይት ማግኘት ትችላላችሁ።

www.seattleschools.org/area/acastan/index.dxml

**ጥቆማ**

- ትምህርትቤቶች ወላጆች ክፍል መጥተው ጉብኝት እንዲያደርጉ ይጋብዛል።
- ወላጆች አስተማሪዎች ምን እንደሚያስተሙሩና የተማሪዎች ስራ ለማየት ወደ ትምህርትቤት ይሄዳሉ
- ወላጆች እና አስተማሪዎች ስለ የተማሪው የትምህርት እድገት እና እንዴት በበለጠ መማር እንደሚችሉ በወላጆች እና አስተማሪዎች ኮንፈረንስ ጊዜ ሃሳባ ለሃሳብ ይለዋወጣሉ ወይም ይወያያሉ።
- ወላጆች እና የኮሚዩኒቲው ማህበሮች ተማሪዎች የቤትስራቸው የሚሰሩበት ጸጥታ ያለው ቦታ ያመቻቻሉ።
- ወላጆች ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ምን እንደሰሩ እና ምን አይነት መጽሃፍ እንዳነበቡ ይጠይቋቸዋል። (በሳምንት አንድ ጊዜ)
- አስተማሪዎች ለተማሪዎች፤ ለወላጆች እንዲሁም ለሌሎች የኮሚዩኒቲው ክፍሎች ስላሉት ስራዎችን እንቅስቃሴዎች ያስታውቃሉ።
- ወላጆች እና ኮሚዩኒቲ ማህበሮች አስተማሪዎች ተማሪዎች ለመርዳት ምን ማድረግ እንደሚችሉ አስተማሪዎችን ይጠይቃሉ።

<u>ሌሎች ሃሳቦች:</u>

- ________________________________________
- ________________________________________



**ጥቆማ**

- አስተማሪዎች ተማሪዎች ጥሩ የአካዳሚክ ውጤት እንዲኖራቸው ተማሪዎች እና ወላጆችን አንድ አይነት ግብ እንዲኖራቸው ያደርጋሉ
- ትምህርትቤቶች የወላጆችና አስተማሪዎች ኮንፍረነስ ወይም ስብሰባ በማዘጋጀት ስለ ተማሪዎች ትምህርት እድገት እና ስለ አድራሻ ችግሮችና ስለ ተለያዩ ችግሮች ይወያያሉ።
- ከ የትምህርትቤቱ ሰራተኞች በኩል በሚገኝ ድጋፍ እና ትብብር መሰርት **ወላጆች** በህዝባዊ ትምህርትቤቶች ስላሉት ስለ ተለያዩ የትምህርት ፕሮግራሞችና ሌሎች አማራጭ የትምህርት አይነቶች እና የተለያዩ ክፍሎች መግለጫና ማብራሪያ እንዲያገኙ ማድረግ
- **ወላጆች** የትምህርትቤቱ የተለያዩ የትምህርት ካሪክለም ለምሳሌ እንደ ስፖርት፤ አርት ስነጥበብ፤ ሙዚቃ እና የተለያዩ የኮሚዩኒቲ እንቅስቃሴዎች የመሳሰሉ ፕሮግራሞች ለማዳበር አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ እድል ይሰጣቸዋል።
- **የትምህርትቤቶች ሰራተኞች እና የኮሚዩኒቲው ማህበሮች** ወላጆች የተለያዩ የትምህርት ግቦች ለይተው እንዲያወጡ ትብብር ማድረግ።
- **ትምህርትቤቶች፤ ወላጆች፤ እና የኮሚዩኒቲው ማህበሮች** አንድ ላይ በጋራ ተባብረው በመስራት በትምህርትቤት ለተማሪዎች ጠቃሚ የሆኑ ጥሩ ፕሮግራሞች እንዲኖሩ ማድረግ።
- **ወላጆች፤ አስተማሪዎች፤ ኮንስላሮችና የኮሚዩኒቲው ማህበሮች** አንድ ላይ በጋራ ተባብረው በመስራት ተማሪዎችን ወደ ኮለጅ እንዲሁም ሌላ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ገብተው ለመማር ጥሩ ዝግጅ እንዲኖራቸው ማድረግ።

<u>ሌሎች ሃሳቦች:</u>

- ________________________________________
- ________________________________________

## 5. የትምህርት ፕላን ለየብቻ ለእያንዳንዱ ተማሪ

### የአካዳሚክ ትምህርት ግቦች

እያንዳንዱ ተማሪ በእድሚያቸው ተመጣጣኝ የሆነ የትምህርት አላማ ወይም ግብ እንዲኖራቸው ይፈለጋል።ተማሪዎች በሚደረግላቸው ድጋፍና ትብብር መሰረት ይህንን አላም ግቡ ላይ ማድረስ አለባቸው።

### ድጋፍ ከትምህርትቤቶች፣ ቤተሰቦች እና ኮሚዩኒቲው ማህበሮች

የትምህርትቤቶች ሪፖርት ካርድ እና የፈተና ውጤቶች ወላጆች፣ አስተማሪዎች የተማሪዎች ግብ ምን ሊሆን እንደሚችል ለማወቅና ለመገመት በጣም ትልቅ አስተዋጽኦ አለው።ድጋፍ ለተማሪዎች በተለያዩ መልክ ሊሰጥ ይችላል ።በተለይ የቤተሰብ ድጋፍ ለተማሪው ትልቅ አስተዋጽኦ አለው።

ወላጆች ስለ ልጆቻቸው የትምህርት ፕላን ለማውጣት እርዳታ የሚፈልጉ ከሆነ ከትምህርትቤቱ፣ ከአስተማሪዎች፣ ከኮንስላሮች እና ሌሎች የትምህርትቤቱ ሰራተኞች እርዳታ ማግኘት ይችላሉ። በስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች ወላጆች በልጆቻቸው በተመለከተ ጉዳይ ላይ በሁሉም ነገር የመሳተፍ ሙሉ መብት አላቸው።



## 3. ሪፖርት ካርድ እና ፕሮግረስ ሪፖርት

### የተማሪ እድገት

የስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች ለሁሉም ወላጆች ስለ ተማሪው የትምህርት እደገት የሚያስረዳ የተማሪ ሪፖርት ካርድ በአመት ውስጥ በተደጋጋሚ ወላጆች እንዲያውቁት ይደረጋል። አስተማሪዎች የተማሪው እድገት የሚለኩት ለተማሪዎች በሚሰጠው ፈተና፣ እንዲሁም የክፍል ስራዎች፣ የቤት ስራዎች እና የተለያዩ ፕሮጀክት ስራዎች በሚያገኙት ጠቅላላ ውጤትና ነጥብ መስረት ነው።

የስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች ፖሊሲ መስረት ተማሪዎች ወደ ሚቀጥለው ክፍል ሊሸጋገሩ የሚችሉት በደረጃቸው የሚፈለግባቸውን አስፈላጊውን የአካዳሚክ ነጥቦች ካገኑ ብቻ ነው።

**ጥቆማ**

- ትምህርትቤቶች የተማሪዎች ሪፖርት ካርድ እና የእደገት ወይም ፕሮግረስ ሪፖርት ለወላጆች ያስታውቃሉ። አስፈላጊ ከሆነም የአስተርጓሚዎች አገልግሎት ይሰጣል።
- ወላጆች መቼ ቀን የተማሪዎች የፕሮግረስ ሪፖርት ካርድ ወደ ቤታቸው አድራሻ እንደሚላክላቸው ያውቃሉ።
- አስተማሪዎች ስለ ሪፖርት ካርዱ ያላችሁን ማናቸውም ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ሁልጊዜ ዝግጁ ናቸው።
- ወላጆች ስለ ሪፖርት ካርዱ ማናቸውም ጥያቄ ካልዎት ስልክ በመደውል ወይም ወደ ትምህርትቤቱ በመሄድ ማነጋገር ትችላላችሁ።
- ወላጆች የአስተማሪዎች ስም ያውቃሉ እንዲሁም እንዴት መገናኘት እንደሚችሉ ያውቃሉ ( በስልክ፣ ኢመይል ወይም ቀጠሮ በመያዝ).
- አስተማሪዎች እና የትምህርትቤት ሰራተኞች ስለ ወላጆች አስፈላጊውን መረጃዎች አላቸው። በቀላሉም ስለ ተማሪው እድገት ከወላጆች ጋር መነጋገር ይችላሉ
- አሰተማሪዎች እና ወላጆች ስለ ተማሪው ድክመት ብቻ ሳይሆን የተማሪውን የትምህርት እድገትና ጠንካራ ጎንን በተመለከተ ከወላጆች ጋር ይወያያሉ።
- ወላጆች እና ተማሪዎች ስለ ሪፖርት ካርድ አንድ ላይ ሆነው ይወያያሉ ስለ አንዳንድ ችግሮችና እንዴት ማሻሻል እንዲሚችሉም አንድ ላይ እቅድ ያወጣሉ።

<u>ለሎች ሃሳቦች:</u>

- ____________________________________________
- ____________________________________________

## 4. ደረጃውን የጠበቀ ፈተና

### ደረጃዎ የጠበቁ ፈተናዎች

በሁሉም ደረጃ ያሉት ተማሪዎች ሁሉ ምን እንደተማሩ ለማወቅና ያላቸውን ችሎታቸውን ለመለካት ፈተና ይሰጣቸዋል።ይህ ማለትም በአገሩ እና በስቴቱ በአጠቃላይ አንድ አይነት ደረጃ ያለው ፈተና እንዲወስዱ ይደረጋል።

- ተማሪዎች ምን እንደሚያወቁና ምን መማር እንደሚገባቸው ለማወቅ
- ወላጆች፣ ትምህርትቤቱና የኮሚዩኒቲው መሪዎች ሁሉ ትምህርትቤቱና ተማሪዎች በስቴቱና በአገሪቱ ከሚገኙት ከሌሎች ትምህርትቤት ጋር ሲነጻጻሩ ያላቸው እድገትን ለውጥ ወላጆች እንዲያውቁት ማድረግ።
- የትኛው የትምህርት ክፍል ጥሩ ውጤት እያሳየ እንደሆነ ለይቶ ማወቅ እና የት ለውጥ ወይም መሻሻል እንደሚያሰፍልግ ለይቶ ማወቅ።

ማንም ህጻን ወደኋል አይቀርም በሚለው ህግ መሰርት (NCLB) የስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች የሁሉም ተማሪዎች የአካዳሚክ ትምህርት ችሎታቸው የሚለኩበት አንድ አይነት መመዘኛ እንዲኖራቸው ህጉ ያስገድዳል። በስያትል ተማሪዎች የዋሰል ፈተና በየአመቱ ማለት ከ ሰዎስተኛ ክፍል ጀምሮ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ደርስ ዋሰል ፈተና እንዲወስዱ ይደረጋል። በፈተናው ተማሪዎች ያገኙት ውጤት ዝርዝር በፖስታ ወደ ወላጆች ይላካል።

ሌሎች በትምህርትቤቶች የሚሰጡ መመዘኛ ወይም መለኪያ ፈተናዎች:

- ዳይናሚክ ኢንዲከተር በዚክ ኤርሊ ሊትረሲ (DIBELS):
  አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ንባብ እና የመጻፍ ፈተና
- ዋሽንግተን ላንጉጅ ፕሮፍሽንሲ ቴስት (WLPT):
  የተወሰነ የእንግልዘኛ ቋንቋ ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች የሚሰጥ ፈተና
- ዲቨሎፐመንታል ሪዲንግ አሰስመንት (DRA)
- ዳይረክት ራይትንግ አሰስመንት (DWA)
- ፐርሊመናሪ ኮላስቲክ አፕቲቱድ ቴስት (PSAT):
  ወደ ኮሌጅ ለመግባት የሚዘጋጁ ተማሪዎች የሚሰጥ ፈተና



**ጥቆማ**

- **ትምህርትቤቶች ስለ ተማሪው የፈተናዎች ጊዜ ና ሰአት ወላጆችን ያስታውቃሉ።**
- **ወላጆች ተማሪዎች ለፈተና ተዘጋጅተው እንዲመጡ ማድረግ፣ በቂ እረፈት እንዲያገኑ፣ ጥሩ ምግብ እንዲመገቡ እና ወደ ትምህርት ቤት በሰአታቸው እንዲመጡ ማድረግ።**
- **ትምህርትቤቶች የዋስል ፈተና ውጤት ወደ ወላጆች በፖስታ ይላክላቸዋል።**
- **ትምህርትቤቶች እና የኮሚዩኒቲው ቡድን የተለያዩ ትምህርታዊ ሰሚናር በማዘጋጀት ወላጆች ስለ የፈተናዎች ውጤት አሰራር እንዲያውቁት ማድረግ።**
- **ወላጆች የፈተናው ውጤቶች በጥሞና ማየት እና ከተቻለም ከላፈው አመት ውጤቶች ጋር ማስተያየት።ማናቸውም ጥያቄ ወይም አስተያየት ካልዎትም ከአስተማሪዎች ወይም ከትምህርትቤቱ ሰራተኞች ጋር መነጋገር ይቻላል።**
- **ወላጆች የልጆቻቸው የእያንዳንዱ ትምህርት አይነት የፈተና ውጤት ዝቅተኛ ወይም ከፍተኛ እንደሆነ ያውቃሉ።**
- **አስተማሪዎች እና ወላጆች ስለ የፈተናዎች ውጤቶች በሚደረገው የወላጆች አስተማሪዎች ኮንፍረንስ ከወላጆች ጋር ይወያያሉ።**
- **ትምህርትቤቶች፣ ወላጆች እና ኮሚዩኒቲ መሪዎች አንድ ላይ በጋራ የትምህርትቤቶች የፈተናዎች ውጤት ይገመግሙታል።ጥሩ ውጤት ላላመጡት የሚሻሻሉበት እቅድ ፕላን ያውጣሉ።**

**ሌሎች ሃሳቦች:**

- ____________________
- ____________________